የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሃያ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፶፮
አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፬ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

21st Year No. 56
ADDIS ABABA,31st July, 2015


**ማውጫ**


አዋጅ ቁጥር ፱፻፲፪/፪ሺ፯ ዓ.ም

ለፈጣን መንገድ ልማት ድጋፍ ፕሮጀክት ማሰፈፀሚያ የሚውል ብድር ከአለም አቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ…………………………………………..ገጽ ፰ሺ፪፻፸፮


**CONTENTS**


Proclamation No. 912/2015

International Development Association Financing Agreement for the express Way Development Support Project Ratification Proclamation ……………...........…...Page 8276


## አዋጅ ቁጥር ፱፻፲፪/፪ሺ፯

## በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በአለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለፈጣን መንገድ ልማት ድጋፍ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ፪፻፷፪ ሚሊዮን ፱፻ሺ ኤስ.ዲ.አር ( ሁለት መቶ ስልሳ ሁለት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሺ ኤስ.ዲ.አር) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በአለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል እ.አ.አ ጁን ፲፰ ቀን ፪ሺ፲፭ በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፴ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ በህገ መንግስት አንቀፅ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሰረት የሚከተለው ታውጇል።

## PROCLAMATION No 912/2015

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE FINANCING AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT

WHEREAS, a Financing Agreement, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the International Development Association Provide to the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Credit amount of 262,900,000 SDR (Two hundred and sixty two million nine hundred thousand Special Drawing Rights) for Financing Express Way Development Support Project was signed In Addis Ababa on the 18th day of June 2015;

WHEREAS the House of people's Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Financing Agreement at its session held on the 7th day of July 2015.

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows.

፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "ለፈጣን መንገድ ልማት ድጋፍ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከአለም አቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፱፻፲፪/፪ሺ፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. <u>የስምምነቱ መፅደቅ</u>

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በአለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል እ.አ.አ ጁን ፲፰ ቀን ፪ሺ፲፭ በአዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር 5625-ET በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

፫. <u>የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ስልጣን</u>

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፪፻፷፪ ሚሊዮን ፱፻ሺ ኤስ .ዲ. አር ( ሁለት መቶ ስልሳ ሁለት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሺ ኤስ .ዲ. አር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሰረት በስራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ስልጣን ተሰጥቶታል።

፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፬ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

1. **<u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as "International Development Association Financing Agreement for the Express Way Development Support Project Ratification Proclamation No 912/2015''.

2. **<u>Ratification of the Agreement</u>**

The Financing Agreement Credit Number 5625-ET signed in Addis Ababa on the 18th day of June 2015 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association is hereby ratified.

3. **<u>Power of the Ministry of Finance and Economic Development</u>**

The Ministry of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Credit amount of SDR 262,900,000 (Two hundred and sixty two million nine hundred thousand Special Drawing Rights) in accordance with the terms and conditions set-forth in the Financing Agreement.

4. **<u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 31st day of July, 2015.**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**